መጽሐፍ ቅዱስ ለህፃናት

አቅራቢዎች



# ልዑሉ እረኛ ሆነ

ጸሐፊው: Edward Hughes
ምሣሌ አቅራቢው: M. Maillot; Lazarus
ያሻሸለው (አሻሽሎ የጻፈው):
E. Frischbutter; Sarah S.
የተተረጎመው: Abel Eshetu
አዘጋጁ: Bible for Children
www.M1914.org

BFC
PO Box 3
Winnipeg, MB R3C 2G1
Canada

©2015 Bible for Children, Inc.
ፈቃድ፡- ይህንን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ማባዛት ወይም ማተም ይቻላል
ነገር ግን ይህ መሆን የሚችለው ለሽያጭ ካላቀረባችሁ ብቻ ነው።



አንድ ቀን ግብጻዊ ሰው አንድ
እስራኤላዊ ሰውን ሲመታ
ሙሴ አየ። ሙሴ ምንም
እንኳ በፈርዖን ቤት
ልዑል ቢሆንም በትውልድ
ግን እስራኤላዊ ነው።
ስለዚህም
እስራኤላዊውን
ሊረዳው
ፈለገ።

ሙሴም አካባቢውን ቃኝቶ ማንም አለመኖሩን አረጋገጠ። ግብፃዊውንም ገደለ። በአሸዋም ውስጥ ቀበረው።



በማግስቱም ሁለት እስራኤላዊያን እርስ በርሳቸው ሲጣሉ አየ። ጥፋተኛውንም "ወንድምህን ለምንድነው የምትመታው" አለው። ያም "ግብፃዊውን እንደ ገደልኸው ልትገድለኝ ትፈልጋለህን?" አለው። ሙሴም፥ ለካስ ያደረኩት ነገር ታውቆአል ብሎ ፈራ። ፈርዖንም ጉዳዩን ስላወቀ ሙሴን ሊገድለው ፈለገ። ሙሴም ከቤት ወጥቶ ሸሸ። ወደ ምድያም አገር ሄዶ ተቀመጠ።



እዚያም እንደ ደረሰ በአንድ የውሀ ጉድጓድ አጠገብ ተቀመጠ። የምድያም ካህን ሰባት ሴቶች ልጆች ነበሩት። እነርሱም ወደ ውሀው ጉድጓድ መጥተው የአባታቸውን በጎች ውሀ ለማጠጣት ገንዳውን ሞሉት።



እረኞችም መጥተው ሲያባርሯቸው ሙሴም ከተቀመጠበት ተነስቶ ተከላከለላቸው። በጎቻቸውንም አጠጣላቸው።





ሴቶቹም ወደቤታቸው ሲመለሱ አባታቸው ራጉኤል (ዮቶር) “ዛሬ ያለወትሮአችሁ እንዴት በጊዜ መጣችሁ?” አላቸው።

ምክንያቱን ሲያስረዱት አባታቸውም “ጥሩት ይምጣ” አለ። ሙሴም ከዮቶር ጋር ኖረ። ዮቶርም ትልቋን ሴት ልጁን ለሙሴ ሚስት አድርጎ ሰጠው።

በግብፅ አገር ንጉሱ ፈርዖን ሞተ። የእስራኤላዊያን ሕዝብ ግን ባርነታቸው ቀጠለ። እስራኤላውያን ከባርነታቸው



ግፍ የተነሳ ወደ እግዚአብሔር አብዝተው ፀለዩ። ፀሎታቸውም ተሰማ።

እስራኤላውያንን ነጻ ለማውጣት
እግዚአብሔር ሙሴን ሊጠቀመው
ፈልጓል። ሙሴ ግን አላወቀም።
ከግብፅ ከወጣ አርባ አመታት
አልፈዋል። አሁን እረኛ ነው።
በግብፅ ያሉትን ወገኖቹን
ግን ይናፍቃል።



አንድ ቀን ሙሴ በቁጥቋጦ መሀል
እሳት አየ፤ ቁጥቋጦው በእሳት ቢያያዝም
እንኳ አልተቃጠለም። ቁጥቋጦው ለምን
እንዳለተቃጠለ ይህን አስገራሚ ነገር
ቀረብ ብዬ ልመልከት አለ።



ሙሴም በቀረበ ጊዜ እግዚአብሔር ከቍጥቋጦው ውስጥ ሙሴ፥ ሙሴ ብሎ ጠራው። እርሱም፦ አቤት አለ። እግዚአብሔርም፦ ወደዚህ አትቅረብ አንተ የቆምህባት ስፍራ የተቀደሰች መሬት ናትና ጫማህን ከእግርህ አውጣ አለው።



ሕዝቤን የእስራኤልን ልጆች ከግብፅ ታወጣ ዘንድ ወደ ፈርዖን እልክሃለሁ። አለው። ሙሴ ግን ለመሄድ ፈርቶ ነበር።



እግዚአብሔር ለሙሴ ታላቅ ኃይሉን አሳየው። የሙሴ
በትር ወደ እባብ ተቀየረች።



ሙሴ እጁን ዘርግቶ አባቧን ሲይዛት እንደገና በትር ሆነች።
እግዚአብሔርም ሌላ ምልክት ሰጠው።



እጁንም ወደ ብብቱ አገባት ባወጣትም እንደ በረዶ ለምጽ ሆነች። እጁንም ወደ ብብቱ መለሳት፤



ከብብቱም ባወጣት ጊዜ ተመልሳ ገላውን መሰለች።



ሙሴም እኔ ጥሩ ተናጋሪ አይደለሁም በማለት ወደ ፈርዖን ለመሄድ ፈቃደኛ አልነበረም። የእግዚአብሔርም ቍጣ በሙሴ ላይ ነደደ። እኔ ወንድምህ አሮንን እጠቀምበታለሁ። አንተ የሚናገረውን ቃል ንገረው አለው።



ሙሴም ወደ ዮቶር ቤት ተመለሰ። ንብረቱን፣ ሚስቱንና ልጆቹን ይዞ ወደ ግብፅ አገር ሄደ።



እግዚአብሔርም አሮንን፦ ሂደህ በምድረ በዳ ሙሴን አግኘው አለው። ሄዶም አገኘው፥ ሙሴም እግዚአብሔር እስራኤላውያንን እንዴት ነጻ ለማውጣት እንዳሰበ ለአሮን ነገረው። ይህንንም ለእስራኤላውያን አለቆች ነገሯቸው። አሮን ተአምራቱን በሕዝቡ ፊት አደረገ። ሕዝቡም አመኑ። እግዚአብሔርም የእስራኤልን ልጆች እንደ ጐበኘ ጭንቀታቸውንም እንዳየ በሰሙ ጊዜ፥ አጐነበሱ ሰገዱም።



ሙሴና አሮን መጥተው ፈርዖንን እግዚአብሔር ሕዝቤን ልቀቅ ይልሃል አሉት።



እርሱም አልለቀም አለ። ፈርዖን ልቡ ደንዳና ነው። ስለሆነም እግዚአብሔር ታላቅ ኃይሉን ሊያሳየው ይገባ ነበርና ብዙ መቅሰፍቶችን በአገሩ ላይ ላከበት።



ልዑሉ እረኛ ሆነ

ይህ ታሪክ የሚገኘው የእግዚአብሔር ቃል
በሆነው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ

ዘጸአት ምዕ. 2-5

“የቃልህ ፍቺ ያበራል.”
መዝሙረ ዳዊት 119:130

መጨረሻ

ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ የሚያስተምረን ግሩም ስለሆነው አምላካችን
እግዚአብሔር እኛን በመፍጠሩ እሱን እንድታውቀው ነው።

እግዚአብሔር "ኃጢአት" ብሎ የሚጠራውን ክፉ ነገር እንዳደረግን ያውቀዋል።
የኃጢአት ደመወዝ ሞት ነው ነገር ግን እግዚአብሔር በጣም ስለወደደን
አንዱንና ብቸኛው ልጁን ለቀራኒዮ መስቀል ሞት አሣልፎ በመሥጠት
እንዲሞትና የኃጢአታችንን ዋጋ በእኛ ምትክ በመሞት እንዲከፍል አደረገው።
ኢየሱስ ከሞት ከተነሣ በኋላ በምድር ላይ ቆይቶ ወደ ሠማይ ወደ አባቱ አረገ!
ያላመንን እኛም በኢየሱስ አዳኝት ብናምን እና ኃጢአታችንን ይቅር እንዲል
ብለምነው ይቅር ይለናል። ደግሞም ያደርገዋል። እሱም በእኛ ውስጥ ይኖራል፤
እኛም በእርሱ ውስጥ ለዘላለም እንኖራለን አሜን።

ይህ እውነት እንደሆነ ካመናችሁ፣ እግዚአብሔርን እንዲህ በሉት
ጌታ ኢየሱስ ሆይ አንተ አምላክ እንደሆንክ አምናለሁ ነገር ግን ለእኔ ኃጢአት
ለመሞት ስትል ሰው ሆንህ አሁን ደግሞ ህያው ነህ። እባክህ ወደ ህይወቴ ግባ
ኃጢአቴን ይቅር በል በዚህም አዲስ ህይወት አሁን ይኖረኛል አንድ ቀን
ከአንተ ጋር ለዘልዓለም ለመኖር ወደ አንተ እመጣለሁ። ለአንተ እንድኖርና
እንደ ልጅ እንድታዘዝልህ እርዳኝ። አሜን።

በየዕለቱ መጽሐፍ ቅዱስን በማንበብ ከእግዚአብሄር ጋር ተነጋገር! የሐ. 3.16